# የፖለቲካ ኤሊኖ በኢህአዴግ

ውድ አንባብያን ሆይ ባለፈው የካቲት ወር 2008 ዓ/ም ላይ ኢህአዴግ ከቸልሲ ምን ይማራል? ህዝቡና ተቃዋሚቸዎችስ? በሚል ሰፋ ያለ ይዘት ያለው ጽሑፍ አቅርቤ ነበር ። ጽሑፉ ለተወሰኑ መገናኛ ብዙሃን ብልከዉም አይጋ ፎረም እና ህብረ ብዕር መጽሔት ላይ ለአንባብያን በመብቃቱ ሃሳቤና ጭንቀቴ ብዙ ሰው እንደተጋራኝና በዛው ልክ ስለመፍትሄው የሚያስብ በርካታ ሰው እንደሚኖር በመገመት ደስታ ተሰምቶኛል። ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ መፍትሔ ለማምጣትም ሆነ ለማጥፋት ሚናው ከፍ ያለ በመሆኑ ጽሑፉ እንዲያነበው የነበረኝ ምኞት ምን ያክል እንደተሳካ ባላውቅም ከአንድ የብአዴን ከፍተኛ አመራር በነበረኝ የሻይ ቡና ቆይታ እሱና የተወሰኑ የአመራር አባላት ማንበባቸው ስለተረዳሁኝ ህዝቡ ለድርጅቱ ውስጣዊ ሁኔታ ያለው እውቀት ምን ድረስ እንደሆነ ሊረዱትና ስለ ዘላቂ መፍትሔ ሊያስቡ ይችላሉ በሚል ተስፋ ደስታየ ከፍ ያለ ነበር። ጽሁፉ በፌስ ቡክ አድራሻየ ያነበበልኝ ታደሰ እሸቱ የተባለ በአካል የማላውቀው የፌስቡክ ጓደኛየ የተወሰኑ ሃሳቦች እንደሚጋራኝ ገልፆ ብዙ መጨነቄን መረዳቱና ብዙ መጨነቅ እንደሌለብኝ ምክሩ አካፍሎኝ ነበር ። በጎንደር ያጋጠመው ችግር ሲሰማ ጭንቀቴ መሬት ላይ መሰረት እንደነበረው ይረዳልኛል ብየ አስባለሁ። ለማንኛውም ይህንን ፅሑፍም ተያያዥነት ያለው በመሆኑ የመጀመርያው ፅሑፍ ለማንበብ አጋጣሚውም ሆነ ግዜው ያላገኛቹ እና ለማንበብ የፈቀዳቹ ሁሉ ይህንን ፅሁፍ ከዛኛው በኋላ ብታነቡልኝ ለነገሮች ትስስር ይጠቅማቹ ይሆን ነበር ባይ ነኝ። ያ 'ጽሁፍ በአይጋ ፎረም Feb 2016 አማርኛው ላይ ወይም በfacebook አድራሻየ selamwerq huluager ብላቹ ብትገቡ ታገኙታላቹ።ለሰጣችሁኝ ትኩረትና ግዜ እያመሰገንኩኝ ወደ ዛሬ ሃሳቤ ከመግባቴ በፊት ጀማሪ ጸሐፊ ከመሆኔ ጋር ተያይዞ ለሚከሰትብኝ የቃላት፣የሰዋሰውና የሃሳብ ፍሰት ችግር ዛሬም በድጋሚ ይቅርታ እጠይቃሎሁ።

**የፖለቲካ ኢሌኖ በኢህአዴግ፤**

ኢህአዴግ ራሱን ከፊል ጨለማ ውስጥ ሲያስገባ ከጨለማው በርግዶ የማምለጥ ልምድና ታሪክ ያለው ድርጅት እንደሆነ ራሱ ከሚናገረው ብቻ ሳይሆን እኛም በሃያ አምስት ዓመታት የጋራ ቆይታችን መታዘብ ችለን ነበር። ድርጅቱ "ከተሃድሶ" በፊት ጀምሮ ካጋጠመው የክራይ ሰብሳቢነት ንቅዘት ለመውጣት ያደረገው መፈራገጥ ግን ራሱንም ሆነ ህዝቡ ከማድማት በስተቀር የፈየደው ነገር የለም ማለት ይቻላል። ይባስ ብሎ ተግባሩም ሆነ አስተሳሰቡ ወዳልተዳረሰባቸው አከባቢዎችና ክፍሎች መዛመቱ ብቻ ሳይሆን ድርጊቱን በድፍረት ሲያወግዙና ሲታገሉ የነበሩ ሰዎች ሳይቀር "ሌላ መንገድ የለም" ብለው ወደዚሁ የጥፋት ጎዳና ሲገቡ ይታያል።የዚህ ችግር መስራችና ዋና አስፈፃሚ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ መሆኑ ደግሞ ፀረ-ክራይ ሰብሳቢነት የሚደረግ ትግል ከባድ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን የአሸናፊነቱ ግምት ለማን እንደምንሰጥ አዳጋች አድርጎታል።

በዚህ ዙርያ ባለፈው ጽሁፌ ተወልጄ ያደግሁባትን የሰሜን ጎንደር ሁኔታ ለአብነት በማንሳት በዝርዝር ለመግለጽ እንደሞከርኩት ችግሩ በህዝብና በመንግስት ሃብት ስርቆት ብቻ የሚገለፅና የሚቆም አልነበረም።ዋና መነሻው ከፖለቲካዊ አቋም መንሸራተት ስለሆነ ደረጃ በደረጃ ወደ ስርዓቱ ጠላትነት በመሸጋገር "ህጋዊ" በመዋቅር ያለ ጠላት በመሆን ከሌላው የለየለት ጠላት በበለጠ ስርዓቱን ገዝግዞ የመጣል አቅሙ ከፍተኛ ይሆናል ። ራሱን ለመከላከል ሲል ማንኛዉም ህጋዊና ህገ-ወጥ አማራጮችን አሟጦ ይጠቀማል። አገር እስከመበተን የሚደርስ አማራጭ ለመጠቀም ወደኋላ ማለት የለም። በድርጅቱ ውስጥ መከፋፈል እንዲፈጠር መጣር፣እሱ ይወክለኛል የሚለው ህዝብ በደል እየደረሰበት እንደሆነ ደጋግሞ በመስበክ ህዝቡ የመበደል ስሜት እንዲያድርበት በማድረግ ህዝቡ ፀረ-መንግስት ወይም ፀረ-ሌላው ህዝብ እንዲነሳ በማድረግ እሱ የህዝቡ ጠበቃ መስሎ ከህዝቡ ቅጣት ራሱን ማዳን፣ አለፍ ካለ ደግሞ መንግስት እንደዛ ዓይነት ቁርጠኝነት ያለው አይመስልም እንጂ መንግስት በወንጀለኛው ኃላፊ እርምጃ ለመውሰድ ሲያስብ ህዝቡ "ጠበቃችን ስለሆነ ብቻ ጉዳት እየደረሰበት ነው" ብሎ በማሰብ ከለላ እንዲሆነው ለማድረግ የቻለው ሁሉ ያደርጋል ። ሌላው ባለፈው ጽሑፌ ደጋግሜ እንደገለፅኩት በመንግስትና በድርጅት ያለው ህጋዊ ኃላፊነት በመጠቀም ደጋፊዎችን መሾምና ተቀናቃኞችን መቅጣት ፣ እሱ የፈለገውን የማድረግ ኃላፊነት ያለው መሆኑ ለቻለው ሁሉ በማዳረስ ብዙ ሰው አምኖም ሆነ ፈርቶ ከጎኑ እንዲሰለፍ በማድረግ ኔትዎርኩን ማስፋት፣ ኔትዎርኩ ከቁጥጥሩ እንዳይወጣ የኔትዎርኩ አባላት በህግ በሚያስጠይቁ ወንጀሎች እንዲሳተፉ በማድረግ ወይም

በተለያዩ መንገዶች ወደሱ ማቅረብ፣ መንግስት ህግ የማስከበር ስራ እንዳይሰራ ማደናቀፍ፣ ከመንግስት ፍላጎት ወጪ ተቃራኒ መግለጫ በመስጠት፣መንግስት መዳከሙን ለወዳጅም ለጠላትም ለማስረዳት በሚችለው ሁሉ የሚያደርግና መንግስት ከችግሩ እንዳይወጣ ከመፀለይ አልፎ ከዚህ አገር ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች በማበርም ጭምር የቻለውን ሁሉ የሚያደርግ ነው። ይህ ኃይል በሴራው ብዙዎቹን እያነካካ አደገኛነቱ እየጠነከረ መጀመርያ ድርጅቱን ይቆጣጠራል ቀጥሎ በአገር ደረጃ በተለያዩ መፎክሮች ከጎኑ መሰለፍ የሚችል ሁሉ እያሰለፈ አገር ይበትናል። ይህ ሁኔታ ከፅንሰ ሃሳብ አልፎ ኢህአዴግ በሚመራት ኢትዮጵያ በተግባር እየታየ ነው። ልብ በሉ የዚህ ሁሉ መነሻ በክራይ ሰብሳቢነት ላይ በወቅቱ እና በተገቢው ሁኔታ እርምጃ ያለመወሰድ ውጤት መሆኑ።

በአገራችን በተለያዩ አከባቢዎች ያጋጠሙ ችግሮች ከላይ ከተገለፁ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሲሆን በቅርበት የማውቀው የሰሜን ጎንደር ሁኔታ ለዚህ በጣም ገላጭ ሆኖ ስላገኘሁት የተወሰነ ዘርዘር አድርጌ ላቅርበው። በቅርቡ በሰሜን ጎንደር ያጋጠመ ግርግር መሰረቱ ወንጀለኞች ይያዙ አይያዙ ከሚል የመነጨ አይደለም። የችግሩ ምንጭ በብአዴን ውስጥ እያቆጠቆጠ ብቻ ሳይሆን እየለመለመና እያበበ ከመጣው የክራይ ሰብሳቢነት ዝቅጠት አደጋ ለመሆኑ የፖለቲካ ትምህርትም ሆነ ፍልስፍና የሚጠይቅ አይደለም። ይህ የአጥፊነት መንገድ ደግሞ በአቶ ገዱ አንዳርጋቸው የሚመራ መሆኑ ነው። አቶ ገዱ በምርጫ 1997 ዓ/ም በባህርዳር አንድ እራት ቤት አብረው ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ የሞያ ባልደረባ ስለነበር እንዳወራኝ ያኔ ኢህአዴግ ለምን በብዙ ቦታ ተሸነፈ የሚል ሃሳብ ተነስቶ በሚወያዩበት ወቅት አቶ ገዱ "ጉዳዩ በአንድ ወይም በሌላ ምርጫ ጣብያ መሸነፍ ሳይሆን ያጋጠመው የጠቅላላ ስርዓት ውድቀት ነው።" በወቅቱ እሳቸው የተጠቀሙት ቃል እንግሊዝኛ ስለነበረ "system faller" ነው ብለው ሲናገሩ ሰምቶ ደንግጦ በተገናኘን ግዜ ሲያነሳልኝ ለምን እንደዚህ አሉ ብለን በወቅቱ ስንገመግም የሰውየው የአቅም ውስንነት እንደሆነ ነበር የፈረጅነው። ሰውየው ከዚህ ችግር የሚያመልጡ ባይሆኑም ዋና መነሻው ግን ከፖለቲካ አቋማቸው በማፈንግጥ ወደ ክራይ ሰብሳቢነት መንገድ መግባት መጀመራቸው ነበር። ከዛ በኋላ "መንግስት የለም" ብለው ያመኑ ሰው ድርጅቱ ወይም ራሳቸው ከኃላፊነታቸው ይነሳሉ ብለን ስንጠብቅ ይባስ ብሎ ኃላፊነታቸው እያጠናከሩ መምጣታቸው አስገራሚ ነበር።አቶ ገዱ ወደ ክራይ ሰብሳቢነት መንገድ ከገቡ በኋላ አንደኛው የክራይ መሰብሰብያ ምንጭ አድርገው መጠቀም የፈለጉት የሰሜን ጎንደር ሰፋፊ መሬቶችን ሲሆን በተለያየ ዋጋ ሲሸነሽኑ ከቆዩ በኋላ በዞኑ ያለ የብአዴን አባል እየተቃወመ እያለ የግብርና ቢሮ ኃላፊነታቸው ተጠቅመው ብአዴን ወደ ልማት እንዲመሩት የሰጣቸው የመሬት አመራርነት እሳቸው ወደ ገበያ አቀረቡትና እንደ ቴሌ ገቢ ገንዘብ ማለብ ብቻ ሆነ።ህዝቡ ከማማረር አልፎ እስከ ፌደራል መንግስት ድረስ የሰሚ ያለ ብሎ ሰሚ ሲያጣ ተደራጅቶ ወደ ሽፍትነት እስከ መውጣት ሲደርስ እሳቸው ከግብርና ቢሮ ኃላፊነት ወደ ክልሉ ፕሬዝዳንትነት ተሸጋገረው ነበር። በዚህ ወቅት ከህዝቡ አልፎ አንዳንድ የብአዴን አመራሮችም ጭምር ስለ ጉዳዩ ማንሳት ሲጀምሩ አቶ ገዱ ከጎናቸው የሚሰለፍ ሰራዊት ማብዛት እንዳለባቸው አሰቡና ከዞኑ አስተዳዳሪ የነበሩ አቶ ግዛት ጀምሮ በዞኑ እስከ ወረዳ ያሉ አመራሮችን በአንድ ለአምስት የኢህአዴግ የህዝብ አደረጃጀት ውድቀት እንደ ተሞክሮ በመውሰድ በአንድ ለሺህ አደረጃጀት የተሳካ የክራይ ሰብሳቢነት የጥፋት ሰራዊት በማደራጀት ለአላማቸው መሳካት የሚያስችሉ መረሀ ግብር በመንደፍ መንቀሳቀስ ጀመሩ።

**ስልቶቹ እንደሚከተለው የተደራጁ ነበሩ፤**

- ✓ የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ በአበልጅነት ከተፈጠረው የግንኙነት ሰንሰለት ውጪ ራሱ ቀደም ብሎ በጀመረው የክራይ ሰብሳቢነት መንገድ አስፋፍቶ በመቀጠል ግለ ሂስ ለማድረግ ወደማያስብበት ደረጃ እንዲደርስ መግፋት ፣
- ✓ አብዛኛው በዞኑ ያለ በማንኛውም የመንግስት ሃላፊነት ያለ ሰው ወደዚሁ እንዲገባና ከዞኑ አስተዳዳሪ ጋር በመሆን "እኛ አለንላቹ" የሚል የልብልብ እንዲሰማቸው በማድረግ በሌሎች ዞኖችም ወሳኝ ቦታዎች ላይ ኃላፊነት እየሰጡ ኔትዎርክ ማስፋፋት ፣
- ✓ "ነባሩ የብአዴን/ኢህዴን አመራር በአብዛኛው ለአማራ ህዝብ ዴንታ የሌላቸውና ይህንን የተከበረ ህዝብን የማይወክሉ ናቸው። ከዛም ባለፈ ለህወሃቶች ያደሩ ናቸው ።እኛ ይህንን ለመቀልበስ ቆርጠን ተነስተናል። ህዋሃቶችን ልካቸው እንዲያውቁ በማድረግ የአማራን ክብር እንመልሳለን" በሚል በመላ ክልሉ በዘረጉት ኔትወርካቸው በመጠቀም ማሰራጨትና በሚያስተዳድሩት ህዝብ ዘንድ እንዲዳረስ ማድረግ፣

- ✓ በብአዴን አመራር ውስጥ ሊታገሉን ይችላሉ ብለው የሚያስቧቸው አመራሮች "እገሌ አማራ ስላልሆነ እንዲህ አደረገ።እገሌ አማራ ቢሆንም እንደነባሩ የብአዴን አመራር የህወሃት አቀንቃኝ ሆኖ የአማራ ህዝብን ክብር የሚነካ ተናገረ ወይም አደረገ እያሉ ማጥላላት"፣
- ✓ "የፌደራል መንግስት የአማራን መሬት ለሱዳን ሸጦታል። እኛ የህይወት መስዋእትነት በመክፈልም ቢሆን እናስመልሰዋለን" የሚሉ ቅስቀሳዎችን ማስፋፋት ዋና ዋናዎቹ ስልቶች ነበሩ።

ከዚህ በኋላ የሰሜን ጎንደር በተለይ የመተማና ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳዎች መሬት ተመን ወጥቶለት ለአንድ ሄክታር መሬት በአንድ ሺህ ብር ግብይት ተጀመረ። ዳግም "የብሎኪንግ ስራ እንሰራለን" በሚል የአከባቢው ህብረተሰብም ሆነ በኢንቨስትመንት ፍቃድ የገባ ባለሃብት ሁሉ የአንዳንዱ ሙሉውን የአንዳንዱ ግማሹን መሬቱ እንዲቀማ አደረጉ።ገበያውም እየደራ ስለሄደ ደላሎችንም የሚጋብዝ ስለሆነ በርካታ ደላሎች በጉዳዩ ላይ እጃቸው አስገቡ። መሬቱ የተቀማ ሁሉ የቀረው መሬት ወደ ሱዳን መሬት ውስጥ ተገብቶ እንዲሰጠው ሲደረግ "መሬቱ የሱዳን ስለሆነ እንዴት እዚህ ይሰጠናል" ያሉትን "ከሃዲ እና የአማራን መሬት ከሸጡት ውስጥ ነህ " እየተባለ በግዴታ እንዲወስድ የተደረገ ቁጥር ቀላል አይደለም።ልብ በሉ የዚህ የመሬት መሸጫ እንቅስቃሴ ስሙ ለሱዳን የተሸጠው የአማራ መሬት "በምርጥ የአማራ ልጆች ገዱና ግዛት" አመካኝነት ማስመለስ ነው።

ሌላው ከላይ ለቀረቡት ስትራቴጂዎቻቸው ማስፈጸምያ ከሆኑት መካከል አንዱ "የወልቃይት ህዝብ አማራነቱ ለትግሬዎች የሸጡት እነ አዲሱ ለገሰ ናቸውና ማስመለስ አለብን" የሚል ስልት ቀይሶ የአማራ ተቆርቋሪነት ስሜታቸው ከፍተኛ እንደሆነ፣ ለህዝቡም ለመዋቅሩም ማስረጽ ነው። ለዚህም ከወልቃይት ከባቢ የአስተዳደር በደል ደረሰብኝ የሚልና ጎንደር የሚሰባሰብ ሰው ሁሉ ጥሩ አቀባበል ከማድረግ አልፎ ለጎንደር ህዝብ ሩቅ የሆነው የመኖርያ ቤትና የእርሻ ቦታ መስጠት፣ቀጥሎ እርስበርሳቸው እንዲሰባሰቡ ማድረግ፣ቀጥሎ ሰዎች እየመረጡ አንድ በአንድ ማነጋገር፣ቀጥሎ ኮሚቴ በማደራጀት ጥያቄ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ቀጥሎ ጥያቄ ስለቀረበልን አዳመጥናቸው ማለት ፣ ቀጥሎ እነ እገሌ የተባሉ የቅማንት ኮሚቴ ጎንደርን እየበጠበጡ ያሉት መቀሌ ቤት ተሰጥቷቸው ከህዋሃት መመርያ እየተቀበሉ አንደሆነ በቂ መረጃ ደርሶናል በማለት ወሬው በክልሉ ሁሉም ቦታ እንዲዳረስ በማድረግ የወልቃይት ኮሚቴ ብለው ያደራጇቸውን ሰዎች በግልጽ ወደ ቢሮ እየጠሩ ቀን በቀን መሰብሰብና አደረጃጀቱ ማስፋት ዋናው የዞኑ የልማት እቅድ ሆኖ ቀጠለ። ይህ ሁኔታ ያልጣማቸው አንዳንድ የብአዴን አመራሮች ሃሳብ ማንሳት ሲጀምሩ በአሸሙርና በቀጥታ የህዋሃት ተለጣፊዎች በማለት እንዲሸማቀቁ ማድረግ ዋናው ስልታቸው በማድረግ አመራሩም አብዛኛው ዝምታ እንዲመርጥና በግዜ ሂደት ንፋሱ እያየ እንዲከተላቸው በተጠባባቂነት ማስቀመጥ የቻሉ ሲሆን ጥቂቱ አሁን ከጎናቸው እንዲሰለፍ ሌላው የቀረው ጥቂት እየተቀለደበትም ቢሆን መቃወሙ የቀጠለ ሲሆን የመጨረሻው ጥቂት ኃይል ደግሞ ዘሩ ተቆጥሮ "የክፉ ቀን መርተህ እዚህ ካደረስከን እናመሰግናለን የክብር እንግዳ ብቻ ስለሆንክ አፍክን ዝጋ" ይህም እንየሁኔታው ከዛ በላይ ሊሄድ ይላል የተባለ ሆኖ እየቀጠለላቹ ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የተጓዙት ርቀት ረጅም ስለሆነና ወደኋላ ለመመለስ በማይቻልበት መንገድ ላይ መቆማቸው ስለተረዱ የፌደራል መንግስት ዝም ብሎ ላያየን ይችላል በሚል ግምት ስለያዙ የጎንደር ህዝብ በተለይ የቆላው አከባቢ ህዝብ ከመሳርያ ጋር ያለው ቁርኝት እና ይህ ህዝብ ማሳመን ከቻሉ ያለው የጀግንነት ታሪክ እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከጥቂቶች በስተቀር የአለም መንግስታት ሁሉ በአንድ ድምጽ እያወገዘው እና ለመከላከል የአብረን እንስራ ጥሪ እያቀረቡ ባለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ ምርጫ 2007 ዓ/ም በሰላም እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ የጦር መሳርያ ቁጥጥር እንዲደረግ እየተሯሯጠ በነበረበት ሁኔታ የጦር መሳርያ ፍቃድ ስለምንሰጥ የሰሜን ጎንደር ህዝብ ተሎ እያስመዘገብክ መሳርያ ታጠቅ የሚል አዋጅ በማስነገር ጎንደርን ወደ ጦር መሳርያ ገበያ ማእከል ተቀየረች። በመሆኑም ከደቡብ ሱዳን፣ከሰሜን ሱዳን፣ከሞያሌ፣ ከቶጎ ውጫሌ፣ከአፋር እንዲሁም ከሌሎች አከባቢዎች የተለያዩ የጦር መሳርያዎች በገፍ ወደ ጎንደር መትመም ጀመሩ ፣ዋጋው ጣርያ ነካ። ይህንን ሁኔታ ሌላ መልካም አጋጣሚ እንደሆነ የተገነዘቡ እነ ግዛትና የዞኑ ፀጥታ ዘርፍ ኃላፊዎች የመንግስትን መሳርያ ከግምጃቤት እያወጡ ገበያ ላይ አቅርበዋል። ይህ ሁኔታ እኔ ወላጆቼ ለመጠየቅ ጎንደር ህጂ በአካል ያየሁት ነው ። በዛን ወቅት በቤተሰቦቼና ህዝቡ በጠቅላላ የነበረው ስሜት "መንግስት ከምርጫው በኋላ ከፍተኛ

ትርስም እንደሚኖር ስላወቀ ነው ይህንን እያለ ያለው" የሚል ከፍተኛ ሽብር ውስጥ የገባበት ሁኔታ ነበር ። የኔም ቤተሰብ ከምርጫ በኋላ ከተማው በዝርፍያ ሊተራመስ ስለሚችል ቤታችን ለመጠበቅ መሳርያ ካልገዛህልን ብለዉኝ እስከመጣላት ደርሰን ነበር።

በነገራችን ላይ ይህ እንኳን ብአዴን/ኢህአዴግ በሚመራው መንግስት በሌላም ይኖራል ብላቹ ስለማታስቡ ከላይ የገለጽኩት ሁሉ በግል ስሜት የተሞላ ወይም ሌላ ፖለቲካዊ አጀንዳ የያዘ ነው ልትሉ እንደምትችሉ እገምታለሁኝ። ብትሉም አይገርምም። ይህ ሁሉ እውነት ለመሆኑ ግን የመጀመርያ ጎንደር ሂዳቹ ብዙ ሰው የሚነግራቹ ነው። ወደዚህ ሁሉ አልሄድም ያለ ደግሞ አርማጭሆ ውረዱ በንጉሱ ዘመን ነበር እንደሚባለውና በሰላሙ ግዜ በየመን ከተሞች ሲደረግ እንደቆየው ጥይት ከባቄላና ከማሽላ ጎን ተዘርግቶ ሲቸበቸብ ታገኛላቹ። እድሜ ለነ ወንድም ገዱና ግዛት አገሬ ጎንደር ከመላ አገሪቱ የተሻለ የነፃ ገበያ ስርአት ዘርግታለች።

ሌላውና በጣም እያስገረመኝ ያለው በእነዚህ አመራሮች የመልካም አስተዳደር ተማሮ አኩርፎ ወደ ሽፍትነት የወጣ በርካታ ሰዎች ከሽፍትነትም አልፈው ኤርትራ ካለው ፀረ-ሰላም ኃይል ጋር ግንኙነት የጀመሩ ሰዎች ሳይቀር "ባለፈው የበደላቹ የፌደራል መንግስት ነበር። እኛ ብንሆንም ከላይ በተሰጠን መመርያ ነው ስለሆነም በኛ አትፍረዱብን" ብለው እርቅ ፈፅመው ሰላም ሆነው መታየታቸው ብቻ ሳይሆን ለዚህ መሰሪ ተግባራቸው መሳርያ ለማድረግ መቻላቸው ነው። ከብዙዎች አንዱ በቅርቡ በቴሌቪዥን ተፈላጊ ተብሎ ስሙ የተጠቀሰው ደጀኔ ማሩ የተባለ ሰው ሲሆን ከዚህ በፊት በመልካም አስተዳደር ተማሮ ኤርትራ ካለው ፀረ-ሰላም ጋር እስከመደዋወል ደርሶ እንደነበር  አንድ የፌደራል ፖሊስ ዘመዴ ነግሮኝ ነበር። ለእስር መፈለግያ ትእዛዝ ሲወጣለት እነ ገዱና ግዛት መልካም አጋጣሚ አግኝተው ለመታረቅና እንዳይያዝ ከለላ እንዲያገኝ በማሰብ የሁለቱ ጠገዴ የድንበር ክርክር "ለሽምግልና ህዝቡ መረጠው" በሚል የኮሚቴ አባል እንዲሆን አደረጉት ብቻ ሳይሆን ሰሞኑን መንግስት አፋልጉኝ ሲል ሰውየው ከነ ሙሉ ትጥቁ ጎንደር ከተማ ሆኖ ታጣቂዎችን አደራጅቶ በግጭቱና በጥፋቱ ዋና አዝማች እንደነበር በአካል የሚያውቀው  የክልሉ ልዩ ኃይል  አመራር  አረጋግጦልኛል።

ውድ አንባብያን ከዚህ ሁሉ እውነታ በኋላ የሰሞኑን የጎንደር ግጭትና ግርግር ከወልቃይት የማንነት ጥያቄ ወይም ከአንድ ሰው መያዝ አለመያዝ ጋር የተያያዘ እንዳልሆነና የግል ጥቅማቸው ለማሳደድ ብለው ህዝቡን እንባ ሳይሆን ደም ካስነቡትና ራሳቸው ባመጡት ጣጣ ገደል አፋፍ ከገቡ በኋላ መንግስት እነሱን ፍለጋ ጠረጋ ሲጀምር ህዝቡ እነሱን የሚደብቅ ጫካ እንዲሆንና ወይም መንግስት  የጫካው ምንጠራ ሲጀምር ከህዝቡ ጋር ሲፋጠጥ ቀድመው ወዳዘጋጁት ቦታ ሄደው በኒዮ ሊበራል ኃይሎች ድጋፍ ተቃዋሚ ሆነው ለመመለስ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ ገዱ ዲያስፖራውን ለማሳመን በሚል ውጭ አገር ሲመላለሱ መከረማቸውና እዛ በሄዱ ግዜ እነ እገሌን አገኙ እየተባለ የሚወራው በራሴ ወይም እኔ በማምነው ሰው ያረጋገጥኩት ስላልሆነ በዚህ ጽሁፍ እንዳለ ላቀርበው አልፈለግኩም።ሆኖም በበቂ የፖለቲካ ጤንነት እንደሌሉ ብቻ ሳይሆን በግላጭ ፀረ-ኢህአዴግ እንቅስቃሴ እያደረጉ ስለመሆናቸው ግን ከእውነት በላይ ሆኖ እያየነው እንገናኛለን።

በአሁኑ ወቅት ጎንደር መንግስት አለ ለማለት በማያስደፍር ሁኔታ ላይ እንደሆነች በተደጋጋሚ አይተናል። አንዳንድ ጥቂት በቆላ ወረዳዎች የሚገኙ ቀበሌዎች መንግስት ማስተዳደር ካቆመ አንድ አመት ሆኖታል ።አሁን ደግሞ የጎንደር ከተማ ህገ-ወጥ ሰዎች ከኤርትራ በላይ የተሻለች መደበቅያ አድርገዋት በነፃነት የሚንጎራደዱባት፣ ከኤርትራ መልእክት ይዘው የመጡ ታጣቂዎች ከህዝቡ ታጣቂ ጋር በመሆን ፒያሳ አጂፕ ላይ ከነትጥቃቸው የሚንቀሳቀሱባት፣የሰው ቤት ተገብቶ በግላጭ የሚዘረፍባት፣መንግስት ያልፈቀደው ሰልፍ በፈለግክበት ግዜ የሚካሄድባት ሆናለች። አንዳንድ የዋህ እነ ገዱ  ጉዳይ ከቁጥጥራቸው ስለወጣባቸው የተጨነቁ ይመስለዋል።ጉዳዩ ያለው ግን ወዲህ ነው። የእነሱ የደስታና የድል ቀን አሁን ነው።ከተቻለ በሁሉም አከባቢ ካልተቻለ ደግሞ በአንድ አከባቢ ክርቢት በመጫር መጀመርያ አከባቢውን ቀጥሎ ክልሉን ቀጥሎ ደግሞ አገርን የማቃጠልና የመበታተን ተልእኳቸው ነው በብቃት እየተወጡ መሆናቸው ግልጽ እየሆነ ነው።  አሁን ባላቸው ድፍረት ላይ የኢህአዴግ ዝምታ ተጨምሮበት እነ ገዱ ለዚህ ለክልሉ የዲያስፖራ ቀን መድረክ አስተዋዋቂ ታማኝ በየነ መድረክ አድማቂ ደግሞ ሻምበል በላይነህ ወይም አርቲስት ፋሲል ደመወዝ "አረሱት መተማ" እንዲሆኑ ወስነው ጋብዘዋቸው ይሆናሉ የሚል ጥርጣሬም ነበረኝ።

ይህ የጎንደርና በክልሉ የተነሳ ግርግር እንዲህ በቀላሉ ስላልገነቡት በቀላሉ የሚቆም እንዳይመስላቹ። ይህንን ጭንቀቴን ያየ አንድ የህግ ባለሞያ በሱ ትውልድ ቦታ [በሰሜን ሸዋም] በፀረ-ትግሬ እንቅስቃሴ ሽፋን ጥቂት የማይባሉ በዞኑ የሚገኙ የብአዴን አመራሮችና አባላት ፀረ-መንግስት እንቅስቃሴ ወደ ህዝቡ እያሰራጩ እንደሆነ የነገረኝ ሲሆን በደቡብ ጎንደርም ተመሳሳይ ሁኔታ መታዘቡን ገልፆልኛል። ይህ እንዲሆንም በቻሉት መጠን እየሰሩ ይገኛሉ። ለዚህ ማሳያም የመንግስት ኃላፊነታቸው በመጠቀም በጎንደር ለተካሄደ ህገ-ወጥ ሰልፍ ቢያምንበትም ባያምንበትም በኮሚኒኬሽን ጉዳይ ኃላፊ አመካኝነት "ህገ-ወጥ ሰልፍ ስለተካሄደ ይህንን ፀረ-ህገ መንግስት ስራ የሰሩ ወደ ህግ እናቀርባለን " ሳይሆን "ሰልፉ ህገ-ወጥ ቢሆኑም ጥያቄያቹ ትክክል ስለሆነ ተቀብለነዋል።" ብለው መግለጫ ሰጡ ።ልብ በሉ ትክክል ተብሎ በክልሉ ሙገሳ የተቸረውና በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የተላለፈለት መግለጫው "ወንጀለኛ መታሰር የለበትም ይፈታ፣ ትግሬ ከተከዜ ወዲህ አገር የለውም።"የሚሉትን እና ሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት መፎክሮችን ላነገበ ህገ-ወጥ ሰልፍ ነው።የሚገርመኝ በዛ እንጂ ሌላው በሰልፉ የሚገርመው "ስለ ኦሮሞ ወጣት እንቆረቆራለን" የሚል ጎንደር ላይ መስማቴ ነው ። እኛ ካስተዳደጋችን ጀምሮ እስካሁን ለኦሮሞ ህዝብ ያለን የተዛባ አመለካከት ኦሮሞዎቹም ጠንቅቀው ያውቁታልና "ዶሮን ስያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" እንደሚሉ እገምታሎህ ።ስለሆነም ተመሳሳይ ህገ-ወጥ ሰልፍ በባህርዳር ፣ ደብረታቦር፣ ደሴና ደብረብርሃን እንዲካሄድ እና ህጋዊነት ለማልበስ እየጠበቅን እንገኛለን እንደማለት ነው የተሰጠው መግለጫ።ይህ በክልሉ የተደረገው የህገ-ወጥ ሰልፍ አድርጉና ህጋዊ እናደርግላቿለን ጥሪ ተከትሎም በባህርዳርና በአንዳንድ አከባቢዎች የከፉ ጥፋቶች  ሲደረጉ እያየን እንገኛለን። ስለ ባህርዳር ሰልፍ ሲነሳ በምርጫ ሰሞን "እያንዳንድህ በራስህ፣በሚስትህና በልጅህ ጦር መሳርያ ግዛ ህጋዊ ለማድረግ ተዘጋጅተናል" ተብሎ የጥፋት አዋጅ እንደታወጀለት ላነሳሁት ሃሳብ ማረጋገጫ ነው። ሰማያዊ ፓርቲ በተደጋጋሚ ሲጠይቅ ሰለተከለከለ በሚል ግዜ ጠብቀው አሁን አገር ቀውጢ በሆነበትና የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ በሚታወጅበት ግዜ ሰልፍ ፈቅደናል ማለት ለዚያውም ፀረ-ሰላምነቱ በተደጋጋሚ ላስመሰከረ ሰማያዊ ፓርቲ መሆኑስ አጋጣሚ ይሆን ?ሌላው የባህርዳሩ ሰልፍ በአማራ ቴሌቭዥን በተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፍ እያለ መፃፉና በተደጋጋሚ መናገሩስ ? አቶ ገዱ ሰልፉ አስመልክተው ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ ሰማያዊ ፓርቲን ፀረ-ሰላም ብለው ለመጥራት ተቸግረው የአማርኛ ቃላት ሲፈልጉ መጨነቃቸውና በተለሳለሰ ቃላት ማለፋቸውስ ? ለማንኛውም በቅርብ ግዜ የአማራ ክልላዊ መንግስት የፌደራል መንግስትን የሚቃወም መግለጫ እንደሚያወጣ አለፍ ካለም "ከኢህአዴግ ራሴን አገለልኩ" የሚል መግለጫ ልንሰማ እንችላለን ።በዚህ አጋጣሚ እነ ገዱ፣እነ ግዛት፣እነ ደሴ ወዘተ እንኳን ደስ ያላቹ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስትደግፉና ስትታገሉ ለቆያቹ ደግኖ ፅናቱን ይስጣቹ እላለሁኝ። በመሆኑም አሁን በክልላችን እየታየ ያለው ችግር የሚፈታው በሰሜን ወይም ደቡብ ጎንደር ወይም ሰሜን ሸዋ ወይም ባህር ዳር ሳይሆን በብአዴን የተሟላ የቀዶ ጥገና ህክምና ሲደረግና ከነርቭ ጋር የተያያዘ የሚመስል ግን ደግሞ የተሻለ ኃኪም በማግኘት ያበጠ አካሉ ቆርጦ በመጣል ብቻ ይመስለኛል። ሁኔታው ወደ ከፋ ደረጃ ካደረሱት በኋላ ሁል ግዜ ቪዛ በእጃቸው ያለ ሰዎች በመሆናቸው ግን በዘመኑ ቋንቋ ላሽ እንዳይሉ አደራ እላሎህ ።እኔ ግን መላ እድሜው፣ ጉልበቱ፣ ህይወቱ እንዲሁም ከአሰርት ሺዎች ጓዶቹ ከፍሎ እዚህ ያደረሰው ዓላማ ተዘርፎ ዚወሰድና ርዕዩ ሲቀለበስ ዝም ማለቱ የት ገባ ምን ዋጠው የሚል ነው።

እኔ ቅርበቴም እውቀቴም ወደ ክልላችን ስለሆነ እውነታውን ለመረዳትና ለመግለፅ ቻልኩኝ እንጂ እንደ ኢህአዴግ እየታየ ያለው የጥገኝነት አደጋ ይህ ነው ብለህ ለመግለፅ  የሚያዳግት መሆኑ  በኔም በሌሎችም ሲገለፅ ከርሟል።ችግሩ አለ ወይስ የለም የሚል አነጋጋሪ ስላልሆነ እሱን ትተን ኢህአዴግ ከችግሩ መውጣት ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው ነው። ባለፈው ፅሁፌ ኢህአዴግ በታሪኩ ከችግር የፀዳ ባይሆንም ከችግር የመውጣት ታሪክ ስላለው ከችግሩ ይወጣል የሚል ተስፋ እንዳለኝ ገልጫሎህ። አሁንም ተስፋየ ሙሉ በሙሉ ተንጠፍጥፎ የደረቀ ባይሆምን እምነቴ ግን የመሸርሸር ሁኔታ አይበታሎህ። ለምን ቢባል ኢህአዴግ በጉባኤው ወቅት ያሳየው ፉከራና ቀረርቶ  በፖለቲካ ችግሮች፣ ምንጮችና መፍትሄዎች በማተኮር በዋናው የችግሩ ፈጣሪ የሆነ ከፍተኛ አመራር ላይ በማተከር ሰበር ዜና ያሰማናል ብለን ስንጠብቅ ወደ ቀበሌና ወረዳ በመወርወር እርምጃ ይወሰድባቸዋል ተብለው የተጠበቁ ሰዎች በሚድያ ቀርበው "እኛ ኢህአዴጎች በክራይ ሰብሳቢነትና ክራይ ሰብሳቢዎች የጀመርነው ትግል አጠናክረን እንቀጥላለን" የሚል መርዶ ነጋሪ ሆነው መጡ ። እኔ የገረመኝ  በርካታ የድርጅቱ አባላትና ህዝቡ ድርጅቱ በክራይ ሰብሳቢነት የሚያደርገው ትግል ለማገዝ አሰፍስፎ በሚጠባበቅበት ሁኔታ ኢህአዴግ ራሱ ትግሉ መግደሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ኢህአዴግ መሪ ድርጅት መሆኑ ይቅርና ህዝቡ

በቻለው ደረጃ ለጀመረው ትግል እንኳን ማገዝ ተሳነው። በብዙ ሰው ዘንድ ኢህአዴግ ጉድለት የመቀበል እንጂ ጉድለትን የማረም ባህሉና ታሪኩ ተቀምተዋል የሚል አስተሳሰብ እየተፈጠረ ነው።የኔም አስተሳሰብ እንደዚሁ እየሆነ ነው።

ኢህአዴግ የገባበት የዝቅጠት ችግር ጥልቀቱ ሩቅ ስለሆነና መውጣት ስለማይቻል ግን አይደለም ከችግሩ መላቀቅ እየተቸገረ ያለው።ችግሩን ከመሰረቱ ለመናድ የተነሳ ቁርጠኛ አመራር ስለታጣ እንጂ። እንኳንስ መንግስትን በኮሚቴና ብዙ አቅም ባላቸው ሰዎች ጣምራ አቅም እመራሎህ በሚል ኢህአዴግ ይቅርና፣እንኳንስ በርካታ  ፀረ-ክራይ ሰብሳቢነት አቋም ያላቸው አባላት የያዘ ኢህአዴግ ይቅርና እንኳንስ ህዝቡ ከጎኑ እንደሚሰለፍ  እርግጠኛ የሆነ የኢህአዴግ መንግስት ይቅርና ናይጀርያን ያክል በተዋረድ ሙስናን እንዳልተፃፈ የመንግስት አሰራር በሁሉም ዘርፍ የተንሰራፋባት አገር ሙሀመድ ቡሃሪ የተባሉ አንድ ፕሬዝዳንት ብቻ "በሙስና ውስጥ የገባቹ ሰዎች ላልምራቹ አይማረኝ" ብለው ተነስተው የቀድሞ ፕሬዝዳንት ጉድ ላክ ጆናታንና አንዳንድ ሚኒስትሮች ጭምር በህግ ለመጠየቅ ቆርጠው ሲነሱና ወደ ተግባር ሲሸጋገሩ በአገሪቱ ህዝቦችና በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ተስፋ እንዲያደር አድርገዋል ። እሱን የሩቁ ተውት በኔ እምነት በኦሮምያ የተንሰራፋው ሙሱና ከናይጀርያው ለይቸ አላየውም ። በአንዳንድ ወዳጆቼ እንደምሰማው በኦሮምያ አንዳንድ ባለስልጣናት ያላቹ ሃብት ለፀረ-ሙስና አስመዝግቡ ሲባሉ ከዚህ በኋላ በሙስና ለማግኘት ያሰቡት ገንዘብ ህጋዊ እንዲሆንላቸው ጨምረው ያስመዘግባሉ የሚል ነው ። ሙሰኛው ተደራጅቶና የመንግስትን መዋቅር ይዞ የፀረ-ሙስና ትግል እንዳይነሳ ልብ በሉ ትግሉ ተጀምሮ ማደናቀፍ አይደለም እያልኩ ያለሁት ትግሉ እንዳይጀመር በሚያደርግበት ሁኔታና ሰውን በስውር እስከ ሞት የመቅጣት ድረስ የሚደርስ እጅ ረጅም ነው በሚባልበት ክልል እንኳን መጨረሻው ምን እንደሚሆን ባይታወቅም በቅርቡ እየሰማናቸው ያሉ እርምጃዎች በተለይ በአዲሱ የሱሉልታ ከንቲባ እየሰማነው ያለ ቆራጥነት ለኢህአዴግ አመራሮች በተለይ ለወቅቱ ጠ/ሚንስትራችን ምን ትምህርት አስተላልፎ ይሆን?

ክቡር ጠ/ሚኒስትራችን ችግሩ ሁሉ በእርሶ ዘመን ስልጣን የተፈጠረ እንዳልሆነ  አውቃሎህ። በተለያዩ መድረኮች ከሚያቀርቧቸው ሃሳቦች በመነሳት ያሎትን ብስለት አደንቃሎህ። ይህንን ደጋግሜ ሳቀርበው የቆየሁ ሃሳብ በመሆኑ የተጋነነና ከእምነቴ የራቀ ሃሳብ እያቀረብኩ ከሆነ ጓደኞቼ ይታዘቡኛል። ነገር ግን አንድ  ነገር አምናሎህ ።እምነቱ የኔ ብቻ አይደለም ።አንድ ሰው የሚለካው በተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች እንጂ በመድረክ ባለው ሃሳብ አይደለም። በተለይ የፖለቲካ አመራር ላይ የተቀመጠ ሰው ደግሞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በሚፈጠሩ ክፍተቶች ላይ ወቅታዊና ለችግሩ የሚመጥን እርምጃ መውሰድ ግድ ይለዋል ። እስዎና የእስዎ መንግስት ግን የቫቲካን መንግስት ወይም የዋልድባ ገዳም አስተዳደር እንኳን ያደርገዋል ተብሎ የማይታሰብ በመንግስት ውስጥ ሆኖ የመንግስት ግልበጣ ለማድረግ የተፈቀደለት ህጋዊ ፀረ-መንግስት ኃይል በመንግስት በጀት እንዲንቀሳቀስ ፍቃድ የሚሰጥ በአለም የመጀመርያ የሆነ መንግስት የኢህአዴግ መንግስት ነው። ጥፋተኛ በጥፋቱ የሚቀጣበት ሳይሆን የሚሾምበትና ከመሾምም በላይ ራሱ ጤነኞችን የሚቀጣበት ሁኔታ ውስጥ ያለ መንግስት ነው ። ከፀረ-ሽብር ፣ፀረ-ሙስና፣ ወዘተ ህጎች ጀምሮ በርካታ የአገር ሉአላዊነትና የአገር ልማት ህጎች የሚያወጣ ግን በአግባቡ የማይተገብር መንግስት ነው።

ኢህአዴግ የውጭ ተፅእኖ በበሳል ትንተና የተመሰረተ አቅጣጫ በማስቀመጥ መመከት የሚችል ድርጅት እንደሆነ ነበር የምናውቀው። አሁን በእነሱ ተፅእኖ በአለም የሌለ የዴሞክራሲ ሊቅ ለመሆን በሚል የአገር ውስጥ ህጎች እስከመጣስ ይሄዳል።በዴሞክራሲ ሰበብ ወንጀለኞች ይፈታሉ፣ በህዝብ ጥያቄ ስም ህጎች ተፈፃሚ ሳይሆኑ ይቀራሉ፣ህገ-ወጥ ሰልፎችና ግንባታዎች ይከናወናሉ፣ ህዝቡ እንዳይቆጣ  ሌላ ግዜ እንጠብቅ ይባላል ፣ የሰራውና ሊደነቅበት የሚገባ ጥሩ ነገር ሳይቀር ሌላ አላማ ባላቸውና በሌላቸው ጋዜጠኞች ተሳስታቹሃል ሲባል አዎ ይቅርታ አስተካክላሎህ የሚል መንግስት ነው ያለው። በቅርቡ ከ12ኛ ክፍል ፈተና መሰረቅ ጋር በተያያዘ ለሁለተኛ ግዜ የተዘጋጀው ፈተና ለመውሰድ በተዘጋጁ ሩብ ሚልዮን ዜጎች ላይ ሌላ ጭንቀት የሚፈጥር ወሬ በፌስ ቡክ መሰራጨቱ ተከትሎ እነዚህ ዜጎች ተረጋግተው እነዲፈተኑ በሚል ፌስ ቡክ መዘጋቱ ከተማሪዎቹ በላይ በርካታ ህዝብ እንዲህ ሰላም የምናገኝ ከሆነ ፌስ ቡክ ለዘላለሙስ ቢዘጋ የሚል እኔም ያልጠበቅኩት ስሜት ተፈጥሮ እያለ ጋዜጠኞች ፌስ ቡክ ለምን ተዘጋ ብለው ለአቶ ጌታቸው ረዳ ጥያቄ  ሲያቀርቡላቸው "በመዘጋቱ ይቅርታ። ይቅርታ የምለው ግን ለይስሙላ ነው" የሚል እንኳን ከአንድ ባለስልጣን ለዝያውም

የመንግስት አፈ-ቀላጤ ከማንም ውሎው መሸታ ቤትና ጫት ቤት ያደረገ ሰውም የማይጠበቅ መልስ ሲሰጡ ሰምቸ አፈርኩ።የሚያፍር ሳጣ እኔ ልፈር እንጂ ምን ላድርግ ወንድሞቼ።

በኛ አገር ያለው የተሳሳተ የዴሞክራሲ ትንታኔና ትግበራ ይሄው ነው። የውጭና የውስጥ የጥፋት ኃይሎች ከአንድ የስምሪት ማእከል ተነስተው የስራ ክፍፍል በማድረግ በዴሞክራሲ ስም መንግስትን ሽባ በማድረግ አገር እንዲበትኑ ኢህአዴግ ፍቃድ እየሰጣቸው ይገኛል። እነዚህ ኃይሎች ወደ ሁለት ይከፈሉና አንደኛው ቡድን አሁንም የዴሞክራሲ ምህዳሩ ጠቧል ብሎ በኢህአዴግ ላይ የተለያዩ ጫናዎች ማሳደር ሲጀምር ኢህአዴግ ህጋዊ የህግ ማስከበር ስራውም ጭምር ለድርድር ሲያቀርብና በውሳኔዎች ላይ ልፍስፍስ አቋም ሲያሳይ ሌላኛው ቡድን ደግሞ መንግስት ህግ ማስከበር አልቻለም ተዳክሟል እንዳውም ምስሉ ነው እንጂ መንግስትማ የለም ብለው ህዝቡ እንዲሸበር ያደርጋሉ። ስለሆነም ኢህአዴግ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ተፈጥሮ መዛባት {ኤሊኖ} ውስጥ ነው ያለው።

ባለፈው ፅሁፌ ለመግለፅ እንደመኮርኮት በኔ እምነት ኢህአዴግ ራሱን ለማጥፋት የወሰነው ባለፈው ያ’ ተአምረኛ ነባሩ ቾአመራር እስከ አሁን ግልጽ ባልሆነ ምክንያት መተካካት በሚል የተወሰነው ውሳኔ አተገባበር ላይ የተከተለው የጥፋት መንገድ ነው። የሚገርመው ኢህአዴግ ከፊቱ የጥፋት እሳት እያምቦገቦገ ቢሆንም አይኑን ጨፍኖ ይህንን ጉዞ ለመቀጠል የወሰነ መሆኑ እያየን መሆኑ ነው። አሁን ስራ ላይ ያለው ነባሩ የኢህአዴግ አመራር ያ’ ተአምረኛ የሚባለው የትላንት፣የዛሬና የነገ ሁኔታ በሳይንሳዊ መንገድ በመተንተን የመተንበይና የመምራት አቅሙ ሚሸሾ ነገ በመተካካት ወጥቶ ስለሚያሳልፈው የተሻለ ህይወት ማሰበና መጨነቅ ስራ አድርጎ የወሰደ ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ ከመጨነቅ አልፎ ለነገየ በሚል ከመንግስትም ሆነ ከህዝብ የሚቦጭቅ ሆኗል። አሁን የመጣው ተኪ አመራር ደግሞ በጣም ብዙ ቁጥር ያለው የአመራርነት ስልጠና የወሰደ ቢሆንም ስለ መጭው ሁኔታ መተንበይ ይቅርና የድርጅቱ ፖሊሲና ስትራተጂ በቅጡ ያልተረዳ ነው። በመሆኑም አሁን ያለው ብዙውን የኢህአዴግ አመራር

- ኢህአዴግ ራሱ ያመጣቸው የአገሪቱ እድገት የሚወልዳቸው ፈተናዎች፣
- የአከባቢውና የአገሪቱ ውጫዊና ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታና ቀጣይ አዝማምያው፣
- የፌደራሊዝም መሰረታዊ ባህሪና ባህሪውን የሚመጥን አያያዝና አመራር እንዲሁም
- በዴሞክራሲ ትርጉምና ተፈጥሮ እንዲሁም በህግ ማስከበር መካከል ያሉ ሃሳቦች የሚረዳ፣የሚተነትን፣የሚመራና ችግሮች ሲፈጠሩ ለመፍታት የሚችል ብቃት፣ዝግጁነትና አንድነት ያለው ሆኖ እየተሰማኝ አይደለም። ይህ ግምቴ ትክክል ከሆነ ኢህአዴግ በኳስ ላይ ቁሞ ኳስ ለመጣወት እየሞከረ ነው ማለት ነው። ኳስ ላይ መቆም ደግሞ ውጤቱ ሁላችን መገመት የምንችለው ነው። ከኤሊኖ በኋላ ላሊና የሚባል ነገር እንዳለ ሰምተናል። ላሊና ደግሞ ሰው፣እንስሳ፣ሰብል፣እንጨትና ጠንካራ ዛፍ እንዲሁም ቤትና ሌሎች ከመሬት በላይ ያለ ሁሉም ነገር ጠራርጎ ወደ አባይ ወንዝ የሚጨምር እንደሆነ ግልጽ ነው።

ያም ሆኖ ከምን ምን ይሻላል እንዲሉ አገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ ልማቷ ቀርቶ አገር ሆና እንድትቀጥል ማድረግ በምንም ምርጫ ውስጥ የሚገባ ስላልሆነ አገር ሆና ለመቀጠል ደግሞ ባለፈውም እንደገለጽኩት ከኢህአዴግ የተሻለ የተደራጀ ኃይል ማግኘት አልቻልኩም። ስለሆነም ለኢህአዴግ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳብ አለኝ፤

1. የመጀመርያው ምክሬ እስካሁን ባለው ሁኔታ የኢህአዴግ አባል ድርጅት ስለሆነና ስለ ነገ አፍን ሞልቶ መናገር የማይቻለው የክልላችን ህዝቦች እጣ ፈንታ እየወሰነ ለሚገኘው ብአዴን ነው። የአገርም ሆነ የህዝባችን የውርደታችን ምንጭ እየሆኑ ያሉ በብአዴን ውስጥ የተሰገሰጉ ብዙ የሚመስሉ ዋነኞቹ 8 ሰዎች ብቻ መሆናቸውና ሌሎች ጀሌ ተከታዮች እንደሆኑ እንኳን አንተ ብአዴን እኛም ውጭ ሆነን እናውቃቸዋለን። ለሰውር ተልእኳቸው ማስፈጸምያ እንዲሆናቸው በማሰብ ይህ በአገሪቱ የመጣው ለውጥ ስሙን ቀይረው የትግሬዎች ነው እያሉ ቸኮሌት ሳይቀር ጣእሙ እሬት ነው ብለው ህዝቡን በማወናበድ ለጥፋት እየማገዱት መሆኑ በተግባር የተረጋገጠ ሆኗል። ስርዓቱና የተገኙ ለውጦች ሁሉ የህዋሃቶች ብቻ ሳይሆን የውድ የአማራ የኢህዴንም ልጆች የከፈሉት መስዋእትነት ጭምር ነው። እነሱ ግን አገር ለመበተን ሊጠቀሙበት ሲፈልጉ ስርአቱ

የአንድ የትግራይ ስርዓት አው እያሉ የሌላው ህዝብ ትግልና መስዋእትነት መና ያስቀራሉ ። ስለሆነም ህዝብን ከህዝብ ጋር በማጋጨት በተለይ የትግራይን ህዝብ ከሌላው ህዝብ መነጠል ሲቻል ብቻ ነው ይህችን አገር መበተን የሚቻለው በሚል ሒሳብ የኢህዴንን ታሪክ የአማራን ህዝብ የትግልና የድል ታሪክ ገደል በመከተት የአማራ ህዝብ ታሪክ ያ የምንወቀስበትን የፊውዳሎች ታሪክ ብቻ ነው እያሉን ይገኛሉ።

ከሁሉም በላይ የሚገርምም የሚያሳዝንም በብአዴን 35ኛ ዓመት የልደት በዓል "መኻታህ ለቀህ ለኛ ለሰጠኽን፣ ከልጆችህ እራት ቀንሰህ ለቀለብከን፣ እንዳንሞትብህ ቁጥራችን እንዳይቀንስ ዘብ ለቆምክልን፣ከልጆችህ ከህዋሃት በምንም ነገር ሳትለየን ሁሉም ነገር ሆነህ ለድል ያበቃኸን የትግራይ ህዝብ እናመሰግንሃለን፣እናመሰግንሃለን አሁንም እናመሰግናሃለን።" የተባለው ህዝብ ከወራት በኋላ የአማራ ጠላት አንተ ነህ፣ አገር የምትበትን አንተ ነህ ስለዚህ መቀጣት አለብህ ተብሎ ባላሰበው ባልዋለበትና በማያውቀው ሁኔታ አገር ሰላም ብሎ አገር ባለማበት ከክልላችን ህዝብ በታሪክ፣በደምና በትግል የተሳሰረን ህዝብ አገር አማን ብሎ በተኛበት በእነ ገዱና ጋሻጃግሬዎቹ አገር ጉድ ያሰባለ ዓይን ያወጣ የፀረ-ህዝብነት ድርጊት ተፈፀመባቸው። የብአዴን አባላት ቁመው የትግራይ ህዝብ ሲደበደብ ሲታይ እኔ እንኳን በአማራነቴ እንዲህ ያፈርኩ ቅን የብአዴን አባላትና የጎንደር ህዝብ ምን እንደሚሰማው መገመት ይቻላል። ለነገሩ እኮ ለዚህ ያደረሱንም ትግሬዎች ብቻ ከሆኑም በታሪክ የሚወደሱና የሚመሰገኑ ሆነው ኢትዮጵያ በእድሜዋ አይታው የማታውቀው ታሪክ ያደረሱ ስለሆኑ በመፃፍም ሆነ ሁከት በመፍጠር የማይፋቅ ታሪክ ሰርተው ግዳጃቸው ጨርሰዋል።

ለማንኛውም ብአዴን በጥቂት ሰርጎ ገቦች አገር የማጥፋት ታሪክ ባለቤት እንዳይሆንና በዚህ አገር ፊት ቆሞ ደግሞ ደጋግሞ ሃፍረት እንዳይከናነብ ራሱን በውስጡ ከተሰገሰጉ የጥፋት ኃይሎች ማጽዳት ለነገ ብቻ ሳይሆን ለዛሬ ማታ የማይባል ስራ ነው። አሁን በአገሪቱ የተከሰተው ችግር ምንጩና ተጠያቂው ብአዴን ብቻ ባይሆንም ያንዥበበው ጥቁር ዳመና እንዲዘንብ በማድረግ አገሪቱ ወደ አዲስ ህይወት እንድትገባ በማድረግ አዲስ ታሪክ የመስራት አጋጣሚው ከፊቱ ቁሟል ።በመሆኑም ዛሬ አዎ ዛሬ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር አለበት።

2. ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት የቅድምያ ቅድምያ አድርጎ መስራት ያለበት በአገሪቱ ያንዥበበ ጥቁር ዳመና ማየት ፣ ማመንና ይህንን ዳመና እንዲገለጥና ሁላችን የምንመኛት ወደ ከፍታ እየተንደረደረች ያለች አገር ወዳሰበእው ደረጃ እንድትደርስ ታሪካዊ ኃላፊነት ወስዷል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከብአዴን ጀምሮ በሁሉም ብሔራዊ ድርጅቶች ደረጃና በግንባር ደረጃ ራሱን ከሙሰኞችና በውስጡ ከተሰገሰጉ የውጭ መልእከተኞች ማጽዳት አለበት። እኔ ባለፈው ፅሁፌና ሌሎችም ከኔ በበለጠ ደጋግመው እንደገለፁት ኢህአዴግ ሙሉ ድርጅታዊ ተሃድሶ ያስፈልገዋል። ከህዝብና ከአገር ጥቅም በላይ ለግለሰቦች ለሚንስትሮች መፍራቱና ክብር መስጠቱ ማቆም አለበት። ሌላው እንተወውና በቅርቡ በነበሩ ክስተቶች ብቻ አንስተን እንወያይ። በርካታ የፌደራል መንግስት ተቋማትና ሚንስትር መስራቤቶች አንዳንዶቹ ከአንድ ዓመትም በላይ በርካታ ሚልዮን የህዝብና የአገር ሃብት ማባከናቸው ዋና ኦዲተር ነገረን። ከዛስ? በአ/አበባ በርካታ ቢሮዎች በሚልዮኖች የህዝብ ሃብት ስብሰባ ባልነበረበት ለስብሰባ አበል፣ በመስራቤቱ በሌሉ መኪኖች የተመዘገበ የነዳጅ ወጪና ፔሮል ውስጥ በሌሉ ሰራተኞች ስም የደመወዝ ወጪ መደረጉ በFBC ሲነገር የሰማነው ከአስር ቀን በላይ አልሆነውም።ከዛስ? በርካታ የፌደራል መ/ቤቶች ዓመታዊ የስራ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ ነው ተባለ።ከዛስ ? በመንግስታችን ከፍተኛ የሆነ የማስፈፀም አቅም ውስንነት አለ ተባለ።ከዛስ ? ከራይ ሰብሳቢነት የኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የስርዓቱ አደጋ ነው ተባለ።ከዛስ ? የሁሉም መልስ ዝም ነው። ለምን ቢባል ለዚህ ሁሉ ምክንያት ኢህአዴግ ከአገር በላይ ለግለሰቦች ክብር ስለሚሰጥና ከህዝብ በላይ ለነሱ ስለሚጨነቅ ነው። አሁን ይህ ሊቀጥል አይችልም ። ምክንያቱም ከኤሊኖ በኋላ ላሊና አለችና ነው። ስለሆነም ከህዳሴ ግድብ፣ከኢንዱስትሪ ፓርኮችና ሌላ ለዚህ አገር ወሰኝ የሆኑ የልማት ፕሮጀክቶች በላይ ወቅቱ የሚጠይቀው የፖለቲካ መረጋጋት እንዲፈጠርና አገር የማዳን ስራ መስራት ነው። ከስራቹ በላይ ቁጥራቹ የበዛው እነደነ አቶ አርከበ ያላቹ የመንግስት አማካሪዎችም የመንግስት የወቅቱ ቱኩረት እዚህ ላይ እንዲሆን አማክሩ። "ልማት ሲመጣ ሁሉም ነገር ፀጥ ይላል" የሚል

አባባል ሁል ግዜ እንደማይ ሰራና ልማት ቢመጣም በአንድ ቀን እንደሚፈርስ በተግባር ያየን መሰለኝ። ጀምሮ ከማንኛውም የልማት ፕሮጀክቶች በላይ በጣም በላይ የአገር ማዳን ስራ ዛሬውኑ መስራት ይጠበቅበታል።

ከዚህ ጋር የተያያዘ ኢህአዴግ በመደበኛ ስብሰባው "የውስጥ ድርጅት ስራ ገመገምኩ" ሲል እንሰማዋለን ። የኢህአዴግ የውስጥ ድርጅት ማለት ከብሔራዊ ድርጅቶች ማየትና ማጥራት ውጭ ውስጠ ድርጅት ማለት የት ነው። ኢህአዴግ የአባል ድርጅቶች ጤንነት ካልገመገመ፣በአንዱ አባል ድርጅት የታየ ችግር እንዲፈታ እጁ አስገብቶ ካላገዘና ድርጅቱ እርምጃ ወስዶ ራሱን እንዲያጠራ ካልሆነ ኢህአዴግ የራሱ ውሳኔ የመወሰን ኃላፊነት ከሌለውና ኃላፊነቱ ካልተዋጣ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑ ቀርቶ እድር ይሆናል። የግንባርና የአንድ ፓርቲ ልዩነት በማቅረብ ፍላጎታቹ ለማሟላት ብቻ አትጠቀሙበት ።

በኔ እምነት አሁን ያለው የአገሪቱ የደህንነት ሁኔታ ከ1984 ዓ/ም ሁኔታ የሚመልሱ አዝማምያዎች እየታዩ ናቸው ባይ ነኝ። ኢህአዴግ የአገሪቱ ደህንነት ለማስጠበቅ ራሱንና መንግስቱን በሚያፀዳበት ግዜ በራሱ ጥፋት በውስጡ ከግለሰቦች በላይ ኃይሎች ድረስ የደረሱ አጥፊዎች ስላሉና በዚህ የተወናበዱ ጤነኞችም ጭምር ከጎናቸው ሊያሰልፉና የማጥራት ስራው ከባድና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ ጥርጥር የለውም። ሌላው ቀርቶ በርካታ የፀጥታ ኃይሎችም ከጎናቸው ሊያሰልፉና ደም እስከ ማፍሰስ ሊደርስ ይችላል።በአገራዊ አስተሳሰብ ሳይሆን በግል ጠባቂያቸው ምስል ለመቅረፅ የሞከሩት የየክልሉ ልዩ ኃይል ከፌደራል የፀጥታ ኃይሎች እስከ መዋጋት ሊሄድ ይችላል። ብሔራዊ የፀጥታ ም/ቤቱ በውስጡ ችግሮች ካሉ በመፍታትና እንደአዲስ ማዋቀር ካስፈለገ እንደ አዲስ በማደራጀት በደህንነት ማስጠበቁና በእርምጃ አወሳሰዱ የጎላ ሚና እንዲኖረው ማስቻል ይጠይቃል። ይህ ብሔራዊ ም/ቤት ከያዘው አገራዊ ኃላፊነት አንፃር በየግዜው ለሚከሰቱ የደህንነት ስጋቶችና ክስተቶች እየተሰበሰበ መወሰንና ማስፈጸም ሊያስቸግረው ስለሚችል ከብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት በታች አንድ ግልጽ የሆነ ኃላፊነት የተሰጠው ቋሚ ኮማንድ ፖስት ሊቋቋምና ስራ ሊጀምር ይገባዋል።

3. የተደራጀና የተጠናከረ የፖለቲካ ስራ መስራት ሁሌም ያስፈልጋል ግን እንዳሁኑ የሚያስፈልግበት ግዜ የለም። ኢህአዴግ በብዙ ነገር ወድቋል ስንል እንደ ፖለቲካዊ ድርጅትነቱ የመጀመርያው ውድቀቱ የፖለቲካ ስራው ውድቀት እንደሆነ አያከራክርም። ይህ ማለት የውስጠ ድርጅት ፖለቲካዊ ሁኔታ በአግባቡ ይከታተል አልነበረም ። በአባላቱና በህዝቡ የሚታዩ የአመለካከት ችግሮች በመለየት ችግሩን የሚፈታ የፖለቲካ ግንባታ ስራዎች አልሰራም። ከዚህ ቀደም በድርጅቱ ታሪክ የምንሰማው በጥቂት አባላት የታየች ትንሽ የአመለካከት መዛባት ካለች በመጀመርያ አስተሳሰቡ የነዚህ ጥቂት ሰዎች ችግር ብቻ ላይሆን ይችላል በሚል እሳቤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ዛሬ በጥቂት ሰዎች ያለ አስተሳሰብ እየተስፋፋ ነገ ድርጅቱን ሊበትን ይችላል የሚል መነሻ ተደርጎ አስር በማይሞሉ ሰዎች ለታየ ችግር አንድ ትልቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ አባላት በሙሉ ለብዙ ቀናት ቁጭ ብለው እንዲወያዩበት ይደረጋል አሉ። በዚህ ሁኔታ ችግር የታየባቸው ሰዎችም ከችግራቸው ይወጣሉ ሌሎችም ከጉዳዩ ትምህርት አግኝተው ራሳቸውን ያጠራሉ። ዛሬ አባላት የሚባሉ ሰኳር ወይም ሌላ ጣፋጭ ነገር በፈሰሰበት ቦታ ዝንብ ሲወረው በሚታይበት አይነት መልከ ብዙ ችግሮች በተግባር እየታየና የድርጅቱን ህልውና አደጋ ውስጥ አስገብቶ እያለም ችግሩን የሚቀርፍ ስራ እየተሰራ አይደለም። ህዝቡ ከድህነት በላይ ጠላት እንደሌለውና በድህንት እንዲዘምት እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያ ኢኮነሚያዊ እድገት ከተሰራው ጥሩ ሊባል የሚችል ስራ ውጪ የሰራቸው ሌሎች ውጤታማ ስራዎች ህዝቡ በሚገባ እንዲያጣጥማቸው፣ ከኋላ ታሪካችን ጋር እያያዘ እንዲያያቸውና ለበለጠ ሰላም ለበለጠ ልማት ለበለጠ የህዝቦች መፈቃቀርና መከባበር እንዲነሳሳ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ በሚያመጣ አኳሃን አልተሰራም። በምርጫ ሰሞን በስመ ቀለም አብዮት ከሚነገር ጥቂት ነገር ውጪ የውጭ ኃይሎች ለምን? በምን ? ሁኔታና በማን ?ይህችን አገር ሊያተራምሱ እንደሚፈልጉ በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ዘልቆ የገባ አይደለም። ከሁሉም በላይ ካለፈው ስርዓት ተያይዞ በመጣውና በአሁን ወቅት በተፈጠረው የተዛባ አስተሳሰብ የተነሳ በአገራዊ አንድነት ላይ የተዛቡ ስሜቶች፣አስተሳሰቦችና ተግባሮች መኖራቸው ተረድቶ ፣ አምኖና ተቀብሎ ይህንን የሚፈታ የፖለቲካ ስራ አልሰራም ።

**ከዚህ ጋር በተያያዘ በአገራችን የሚድያና የህዝብ ግንኙነት ስራ ላይ ያለኝ ትእዝብት፤**

በአሁኑ ግዜ ሚድያ በአለም አቀፍ ደረጃ እየፈጠረው ያለ ተጽእኖ ከማንኛውም ኃያላን መንግስታት በላይ መሆኑ እያየነው እንገኛለን። ይህ ተጽእኖ ደግሞ ለጥፋትም ለልማትም መሆኑ ግልጽ ነው። በታሪክ ሶስት አስርተ አመታት ያልሞላው የሩዋንዳ እልቂት ላይ ሚድያው የተጫወተው የአጥፊነት ሚና ከምንም በላይ ነበር። በአለማችን የተካሄዱ የቀለም አብዮቶች መጨፋጨፍ ዙርያ ሚድያ ቀዳሚ ስፍራ ነበረው። ይህ በቅርብ አመታት የአረብ አብዮት ተብሎ የተቀጣጠለው አመጽ አገራቱን ወደ አሸዋ የቀየረ ወይም የአሸባሪዎች መፈንጫ ሆነው እንዲቀሩና መመለስ አይቻልም እንጂ ህዝቡን ለፀፀት የዳረገው "አብዮት" ዋና መሳርያው ሚድያ ነበር። በአገራችን ተከስተው የነበሩ አመጾችና facebook {ፌስቡክ} የነበረው ሚናም የምንረዳው ነው። ስለሆነም የግሎባላይዛሽን ትሩፋትን ለክፋት ለመጠቀም ወስነው ከገቡ የጥፋት ኃይሎች ውጭ መንግስትም ሆነ ሌላው የግል ሚድያ አያያዛችንም ሆነ አጠቃቀማችን ላይ በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት ከበቂ በላይ ማረጋገጫ ናቸው ።ከዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ በግሉ ሚድያ በተለይ ጥቂት ቢሆኑም ለሁሉም ተደራሽ በሆነው ኤሌክትሮኒክስ ሚድያ ዙርያ አከባቢ አንዳንድ ግዜ በተቃዋሚ አስተሳሰብ ውስጥ ገባ ወጣ ሲል አያለሁ።

በኢህአዴግ የፖለቲካና የህዝብ ግንኙነት ስራ ባለኝ ትእዝብት ስጀምር ስራው የመንግስትን አንድነትና የተደራጀ አመራር በመስጠት ረገድ ጥያቄ ውስጥ እያስገባ ያለው የሚድያ ስራው ነው። የመጀመርያው ችግር ሚድያው በተለይ ቴሌቪዥኑ ማራኪ አቀራረብ ስለሌለውና የፀረ-መንግስት ኃይሎች ፀረ-ሚድያው ቅስቅሳ ተጨምሮበት የሚያዳምጠው ህዝብ ቁጥር አነስተኛ እየሆነ ነው። በተለይ ደግሞ ሚድያው በተከታታይነት መያዝና ማስተማር ያለበትን የወጣቱን ክፍል ነው እያጣ ያለው። ስለሆነም የመጀመርያው ጥያቄየ የመንግስት ሚድያው በተለይ የቴሌቭዥኑ ማህበራዊ መሰረት እየተናደ እየሄደ መሆኑ ትረዱታላቹ ወይ ? ነው። ቀጥሎ ታድያ ለምን አይሻሻልም ነው።

የመንግስትም ሆነ የግሉ ሚድያ የሚመራበት ፖሊሲ እንደሚኖር ስለማያጠራጥር ሚድያው በፖሊሲ እየተመራ ስልመሆኑ የሚከታተል አካል አለ ወይ? ግን ያጠያይቃል። ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሆነኝ የመንግስት ሚድያ ወስጀ ስከታተል የአንድ መንግስት ሚድያ እስከማይመስል ድረስ እርስ በርሱ የሚጣረስ ብቻ ሳይሆን በመንግስት ሚድያ ፀረ-መንግስት መልችክቶች ሲተላለፉበት እንሰማለን ። በክልላችን አንድ የፖለቲካ ትኩሳት ሆኖ የከረመው የወልቃይት ጉዳይ ሲሆን የሰሞኑ የጎንደር ግጭት ምክንያት ባይሆንም እንደምክንያት ሲነሳ ሁላችን ሰምተናል። በክልሉና በፌደራል መንግስት ባሉ የክልሉ ተወላጅ ፖለቲከኞች ነን ባዮችና አርቲስቶች ግን ከአስር አመት በላይ ሲሰሩበት ሁላችን እናውቃለን ።ታድያ ይህንን የወልቃይት ጉዳይ በህዝብ ዘንድ የጎንደር እንደሆነች ለማለማመድ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመንግስት ሚድያ ሲነገር ቆይቷል።እድሜ ለወልቃይት ይሁንና አገሬ ጎንደርም ወልቃይት ለመጥራት በማለት ብቻ በአራት አመታት ዉስጥ ብቻ 21 ዘፈኖች ተዘፍኖላት ዘፈኖቹ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እየተደጋገመ ስለቀረበ ጎንደር ደምቃ ከርማለች። በነገራችን ላይ ወልቃይት በታሪክና በህገ-መንግስቱ አንጻር ወዴት መከለል እንደነበረባት ሙሉ መረጃ መያዝ ስላልቻልኩ በዚሁ ዙርያ አስተያየት የለኝም ። በደርግ ዘመን ክልሏ ከማን ነበር ከሆነ ከጎንደር ዳባት ጋር እንደነበረች አውቃሎሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ግን ቸ ወልቃይቶች በደርግ ዘመንም ሆነ አሁን ትግርኛ ተናጋሪ እንደነበሩ አውቃሎሁ። በደርግ ጎንደር ከነበረች በቃ ጎንደር ናት እንዳልል በፖታሽ ማአድን የበለጸገው የአፋር መሬት የትግራይ ነበርና አሁን የትግራይ ሆኖ እያየሁት አይደለም ።ሌላው በደርግ ዘመን የተወሰነ የአፋር ክፍል ከወሎ ጋር እንደነበር አውቃሎህ ። አሁን በአማራ ክልል እንዳልሆነ ደግሞ እያየሁኝ ነው። ለማንኛውም ግን አሁን ያለው አከላለል የሚጻረሩ ዘፈኖችና መልእክቶች በመንግስት ሚድያ መስማት የተለመደ ነው። ከዘፈን ውጭም አንድ ቀን የብአዴን አመራር የሆኑ አቶ አባተ ስጦታው ከአ/አበባ ወጣት የብአዴን አባላት ጋር ውይይት ሲያደርጉ "በወልቃይት መንገድ ያልሰራነው የቦታ ርቀት ስለገደበን ነው። " የሚል ሃሳብ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ሲተላለፍ ሰምተናል። የአቶ አባተ የአፍ ወለምታ አይመስልም ኤዲት ያደረገው ጋዜጠኛም እንዲሁ።ከዚህ ከወልቃይት ጋር በተያያዘ ECX በየቀኑ የገበያ ሁኔታ ሲያቀርብ መጀመርያ ፈራ ተባ እያለ አንድ ቀን የሁመራና የጎንደር ሰሊጥ ብሎ ዋጋ ያቀርባል። አንድ ቀን ደግሞ የሁመራ ጎንደር ሰሊጥ ብሎ ማቅረብ ሲጀምር በሂደት የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ባለቤት እንደሌለው ሲያረጋግጡ ዛሬ ሙሉ በሙሉ ሁመራ ጎንደር በሚል እየቀረበ ነው። የመንግስት ሚድያው መንግስት በባለቤትነት እያስተዳደረው እንዳልሆነ የሚያጠራጥሩ

ምልክቶች በኦሮምያ አመፅ ወቅት ህዝቡን የሚያረጋጉ ስራዎች እንደመስራት የግጭቱ የእለት ከእለት ዉሎ ሁኔታ እየዘገበ በኢሳት እየቀረበ ያለው ትክክል ነው።ኢሳት አይዋሽም የሚል የግንቦት 7 ቃል አቀባይ ሆኖ ሲሰራ ነበር።

በሌላ በኩል በመንግስት ሚድያ ላይ የአየር ሰዓት ገዝተው የተለያየ ዝግጅት የሚያቀርቡ አዘጋጆች አሉ። በአብዛኛው ለተቋቋሙበት ዓላማ ብቻ የሚሰሩ እንደሆኑ እሰማሎህ። አንዳንዶቹ ከመንግስት ክፍያ ጠይቀው ወይም ስፖንሰር ሲደረጉ ብቻ ሊያስተላልፉት ይገባ የነበረ ለህ/ሰቡ የሚጠቅም መልእክት "አገራዊ ግዴታችን ነው።"በሚል የተለያዩ አንድነትን፣ልማትንና ብልጽግናን ሲሰብኩ የሚውሉ በተደጋጋሚ ሰምቻሎህ። በሌላ መልኩ ጥቂት አዘጋጆች በተለያዩ ዝግጅቶች ስም እያዋዙና በመሃል እያስገቡ ፀረ-መንግስት አቋም ሲያራምዱ እናዳምጣለን። መንግስትን በመንግስት ሚድያ መቃወም የተከፈለስ ቢከፈል ተገኝቶ ነው። እኔ እርግጠኛ የሆንኩት ግን የመንግስትን አቋምና ፖሊሲ በህዝብ ዘንድ ዘልቆ እንዲገባ እና ህዝቦች በጋራ እንዲረባረቡ እንዲነሳሱ እንዲያደርግ የሚድያ ኃላፊ ሆኖ የተመደበ ሰው ይህ ሁሉ አይሰማውም ወይም ቢሰማውም ለሱ የሚሰጠው ፖለቲካዊ ትርጉም ከኛ ከህዝቦች በታች ነው።ታድያ ኢህአዴግየ ደግሞ ኃላፊ መድቤሎህ ይላል።

ስለሚጣረሱ ዘገባዎች ብዙ በጣም ብዙ ማለት ይቻላል። አንድ የመንግስት ተቋም ኃላፊ ያቀረበው ሃሳብ ተመሳሳይነት የስራ ዘርፍ ያለው የሌላ መ/ቤት ኃላፊ በተቃርኖ ይገልፃል። ሩቅ በመጓዝ እንዳላሰለቻቹና አሁን ከቀናት በፊት ማለትም በ25/11/2008ዓ/ም ከቀኑበ 6;05 ስአት በሸገር ሬድዮ የአ/አበባ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ስ/አስከያጅ ሆነው ለረጅም ግዜ ያገለገሉ እንጅነር ፈቃደ ኃይሌ በፍቃዳቸው በማመልከቻቸው ከኃላፊነት ተነሱ ስለ መባሉ ገልጾ እሳቸውም በስልክ መስመር ገብተው ጠይቀው ተፈቅዶላቸው  በፍቃዳቸው ስራቸውን መልቀቃቸው ነገሩን፣ በተመሳሳይ ቀን ከአስር ደቂቃ በኋላ ከቀኑ6;15 ስዓት የመንግስት ሚድያ የሆነውFM 96.3 የአ/አበባ መንገዶች ባለስልጣን ዋና ስ/አስፈጻሚ እንጅነር ፍቃደ ኃይሌ በትራፊክ አደጋ መቀነስ ዙርያ መልእክት አስተላለፉ የሚል ዜና አሰምቶናል። ከምሽቱ 12;00 ስዓት fana FM  እንጅነር ፍቃደ ኃይሌ በመንግስት ከኃላፊነታቸው የተነሱ መሆኑና በሂደት በህግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ ገለጸልን። በነገራችን ላይ በየካቲት ወር ጽሁፌ የከፋ ሙስና  ከሚፈጸምባቸው መ/ቤቶች ውስጥ ማሳያ ብየ ከገለጽኳቸው ከአራት ያልበጡ መ/ቤቶች አንዱ የአ/አበባ መንገዶች ባለስልጣን መሆኑ መግለጼ ታስታውሳላቹ።

የሸገር ሬድዮ አዳምጣሎህ። ከሞያ አንጻር ጋዜጠኞቹ ያላቸው ብቃትም አደንቃሎህ። አንዳንድ ግዜ ከመንገድ የመውጣትና የተቀዋሚ ኃይሎች መሳርያ ሊሆኑ የሚችሉ ዝግጅቶች ሲቀርቡበት እሰማሎህ።ለምሳሌ ብንጠቅስ በምርጫ ሰሞን በሸገር ሸልፍ የቀረቡ ዝግጅቶች በአብዛኛዎቹ በሌላ ግዜ ቀርበው የማያውቁ የመንግስትን ድክመት አጉልቶ ለህዝብ ለማሳየት ታስቦባቸው የሚቀርቡ የሚመስሉ ነበሩ። ኃላፊነት የሚወስደው ጻሐፊው ስለሆነ በህትመት ውጤት ስም ኢህአፓን የሚቀሰቅሱ ጽሑፎችን በተደጋጋሚ ሰምቻሎህ። ሌላው በሞያዋ ብቃት የማደንቃት ጋዜጠኛ መአዛ ብሩ በቅዳሜ ጨዋታ ፕሮግራም እንግዳ አድርጋ ካቀረበቻቸው እንግዶች መካከል በኔ ግምት አርባ ከመቶ የሚሆኑቱ የኢህአፓ ታሪክ ያላቸው ሲሆኑ የኢህአፓ አባላት የነበሩ የኢህአዴግ ባለስልጣናትም እንዲሁ። ዋናው ነገር መጋበዛቸው ሳይሆን ሰፊ ግዜ ተወስዶ በተመስጦና በፍቅር ውይይት የሚደረግበት አጀንዳ ያ ጉደኛ ዘመን ነው።

ሌላው ከሁለት ሳምንት በፊት ገደማ በሚድያው በቀረበው የዜና ዘገባ የወጣቶች የክረምት በጎ አገልግሎት ወደ መንግስት የተጠጋ ነው ተብሎ ይታማል የሚል ነበር ።አስቡት እነዚህ ወጣቶች የፖለቲካ ድርጅት አይደሉም፣ የግል ሚድያም አይደሉም፣ የህዝብ አገልግሎቶች የተሰማሩ ተማሪዎች ናቸው። በምን አይነት አገልገሎት እንደተሰማሩም እያየናቸው ነንና ዜናው አስገራሚ ነበር። አስቅኙ ነገር ግን ሸገር ያሳሰበው ለሁለት ወራት የትራፊክ ስራ የማሳለጥ  በመሰማራት፣ችግኝ በመትከል፣የአከባቢ ጽዳት በማስጠበቅና ከነሱ ዝቅ ያለ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ተማሪዎች ትምህርት በመስጠት የተሰማሩ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ለመንግስት ቅርበት አላቸው የሚል የዜና አርእስት ሆኖ በአገር ጉዳይ አሳሳቢ ሲሆኑ በበጎ አድራጎት ማህበራት ስም ተደራጅተው ግልጽ በሆነ መንገድ ወደ ተቃዋሚ ጎራ መቀላቀላቸው ብቻ ሳይሆን በግልጽ የውጭ ኃይሎች

የአገር ማጥፋት አጀንዳ ጉዳይ አስፈጻሚ በመሆን እየሰሩ የሚገኙት ግን በሸገር ብዙም አሳሳቢ አይደሉም የሚል መልእክት ነው የነገረኝ።

ያም ሆነ ይህ ጋዜጠኞች አገር ለማልማት ህዝቡ እንዲነሳሳ በማድረግም ሆነ ህዝቡ በተሳሳተ መንገድ ነገሮች ተረድቶ አገር ለማፍረስ እንዲነሳ ለማድረግ እኩል እድልና ችሎታ አላቸ ። በመሆኑም አገር ከፈረሰች በኋላ እንደ ሊብያና የመን ህዝቦች ተፀፅታቹ ላትመልሷት ነገር የመፍትሄው እንጂ የችግሯ አካል እንዳትሆኑ።አውቃሎህ አንዳንዶቻቹ የሌላ አገር ዜግነት አላቹ፣አውቃሎህ የኒዮ-ሊበራል ኃይሎች አገር በማፍረስ አስተዋጽኦ ላደረገ ጋዜጠኛ በፕረስ ነጻነት ተሚጋች ስም እንደሚሸልሙና ተሎ ጥገኝነት እንደሚሰጡ ቢሆንም እናንተ አሁን ተራ ጉዳይ መስሏቹ የጥፋት ኃይሎችን ጭሆት በማስተጋባት ህዝቡን በማሳሳት አገሪቱን ወደ ጥፋት እንዳታመራ አግዟት ብያንስ የእናት፣አባት፣እህትና መንድሞቻቹ መኖርያ ናት።

አሁን ባለው ሁኔታ በአገሪቱ በሁከትና ረብሻ በመፍጠር የሚገኘው ውጤት የኢህአዴግ መንግስት መጣል እንደሆነ የሚያስብ የዋህ ብዙ እንደሆነ ተረድቻሎህ ። የኢህአዴግ መንግስት ማለት በየቦታውና በየእርከኑ በአስተዳደር ዘርፎች በምናያቸው አስተዳዳሪዎች ብቻ የሚገለፅ አይደለም ። የኢህአዴግ መንግስት መከላከያ ከነ የኋላ ታሪኩ፣ የፌደራል ፖሊስ ከነ የአመራሩ ታሪክ እንዲሁም የመረጃ ክፍሉና ሌሎች የህግ አስከባሪ አካላት ጨምሮ ነው።በዚህ ሁኔታ ኢትዮጵያን አንድ ላደርጋት እችላሎህ የሚል ሌላ ኃይል ሊኖር አይችልም። አያደርም እንጂ እነዚህ የፀጥታ ኃይሎች ዝም አሉና የነውጥ ኃይሎች አንዳንድ ክልሎች ተቆጣጠሩ እንበልና ከኢህአዴግ ጋር ያላቸው መሰረታዊ የአላማ ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ በምርጫ ወደ ስልጣን የመጡ የደቡብ ፣የትግራይ፣የአፋር፣የኢትዮጵያ ሱማሌ ወ.ዘ.ተ መንግስታት በሁከት ወደ ስልጣን ከመጣ መንግስት ጋር መንግስት ሊመሰርቱ አይችሉም። ስለሆነም ኢትዮጵያ የምትባል የብዙ ክልሎች አገር አትኖርም ማለት ነው።ስለሆነም ሁከትና ብጥብጥ የሚፈይደው ነገር ካለ እውነት መስሏቸው ቤተሰቦቻቸው ያለ ጧሪ በማስቀረት ወደ እሳት ተማግደው የሚቀሩ ዜጎች ቁጥር መጨመርና ይህንን እንዲሆን ሲጸልይ የሚያድረው የሁማን ራይት ዎች የሪፖርት ገጽ ማብዛት ብቻ ነው የሚሆነው ።

4. የፀጥታ ኃይሎች ማለትም የመከላከያ ኃይሉ፣የፌደራል ፖሊስ፣ የየክልሉ ፖሊስና ልዩ ኃይሎች በተመለከተ የህ/ሰቡ አካል እንደመሆኑ ተወደደም ተጠላም በየክልሉ በሚኖር የፖለቲካ ሁኔታዎችና በየብሔሩና ብሔረሰቡ በሚታዩ በጎና በጎ ያልሆኑ ስሜቶችና አመለካከቶች ተጽእኖ ውስጥ መውደቁ የግድ ይላል። እስከአሁን ባሉት ክስተቶችም እዛም እዚህም ይህንን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች እታዘባሎህ። ከሁሉም በላይ የታጠቀ ኃይል ከመሆኑና አንድ ላይ የተሰባሰበ ኃይል ከመሆኑ አንጻር አመራሩን በየግዜው ከመፈተሽ ጀምሮ እንደየ አስፈላጊነቱ ሹም ሽር እያደረጉ ቋሚ የሆነ የፖለቲካ ግንባታ ስራ መስራት ግድ ነው። ድሮ በረሃ እያላቹ በየአደረጃጀት እርከኑ የፖለቲካ ስራ የሚሰሩ አደረጃጀቶችና ይህንን ለማስፈጸም የተመደቡ ኃላፊዎች እንደነበሩ እሰማሎህ። በዛ ዘመን ለነበረ የተለየ ህዝባዊ ኃይል እንኳን የቀን ተቀን የፖለቲካ ግንባታ ያስፈልገዋል ተብሎ ሲደረግ የቆየ በአሁን ዘመን፣አሁን ባለው ፖለቲካል ኢኮነሚ ፣አሁን ባለው የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱ ኃይል የቀን ተቀን የፖለቲካ ስራ ከማስፈለግም በላይ ነው ።በመከላከያ ኃይላችን ሁሌ ከምንኮራበት የድል ታሪኩ ሌላ በሙስናና በሃብት ብክነት ከሚታሙ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው። በዚህ ሁኔታ ነገ የሲቭል አስተዳደሩ አገሪቱን መምራት ስላልቻለ ለአገር ደህንነት ብየ ስልጣኑ ለህዝብ ለማስረከብ ብለን ፖለቲካዊ ስልጣኑ ተረክበነዋል እንደማይለን ምን ዋስትና አለን። የፖለቲካ አመራሩ ሰሞኑን በቱርክ ያጋጠመው ከ9000 ወታደሮች ከነዚህ ውስጥ ከ60 በላይ ጀነራሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ታንኮችና የጦር አውሮፕላኖች ያሳተፈ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተደርጎ መንግስት በአንድ ቀን እንዳከሸፈው ለማክሸፍ ይቅርና የጎንደር ከተማ የወጣቶች ግርግር እንኳን መቆጣጠር አልቻለም።

5. ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢህአዴግ የተለያዩ የሊግ አባል ማህበራት ከዚህ ባልተናነሰ ክትትልና ግንባታ ያስፈልጋቸዋል የሚል እምነት አለኝ። እነዚህ የሊግ አባላት በተለይ የወጣቱ ሊግ አባላት በውስጣቸው በዘመኑ ትውልድ ውስጥ ይታያል ብለን የምንለው በአጭር መንገድ ወደ ስልጣንና ወደ ገንዘብ የመቆናጠር አባዜ ያላቸው ይኖራሉ ብሎ መውሰድ አለበት። ኢህአዴግ

ደግሞ እንኳን ለሊጉ ለራሱ የውስጥ ድርጅት ማጥራትና ግንባታም ግዜና ቁርጠኝነት አጥቷል። በመሆኑም የእነዚህ ሊጎች ግንባታ ጉዳይ ኢህአዴግ አስቦ ካልሰራበት የANC የወጣት ሊግ የአሁኑ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት መፈንቅለ ድርጅት ለማድረግ እንደተጠቀመበት ይሆናል ማለት ነው።

6. ነባሮቹ በመተካካት እንበለው በመጠፋፋት  የተቀነሱት አመራሮች ያላቸውን አቅም ለአገር ግንባታ ለመጠቀም እና አሁን ባለው  አመራር እየታየ ያለው የአመራር ክፍተት ለመደገፍ እንዲችል እንደ የአማካሪ ኮሚቴ እንበለው ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ራሳቸው በማደራጀት ድርሻቸው እንዲወጡ ቢያደርጋቸው ኢህአዴግ አሁን እያደረገው ባለው እንቅስቃሴ አንድ ቀዳዳ ይደፍን ነበር የሚል እምነት አለኝ።
7. ሌላው የአገራዊ ደህንነታች ስጋት ከሆነው አንዱ የኤርትራ መንግስት ነው። በኤርትራ መንግስት ብዙም ከፉከራ ያላለፈው የተመጣጣኝ እርምጃ ጉዳይ ትርጉም ባለው ደረጃና የኤርትራን ህዝብ ለለውጥ በሚያነሳሳ መንገድ እንዲካሄድ ማድረግ ሌላው ኢህአዴግ ለብሔራዊ ደህንነታችን ማስጠበቅያ መንገድ አድርጎ መጠቀም አለበት የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ ጎን ለጎን እና ግዜ በማይሰጥ ሁኔታ አሁን ካለው የሁሉም ዓይነት የፖለቲካ ድርጅቶች ነን ባዮች ትርምስ የፀዳ ኤርትራዊ ዴሞክሪያሲያዊ ተተኪ ኃይል እንዲፈጠር መስራት አለበት ባይ ነኝ።

አንተ የኢህአዴግ አባል ካልሆንክ ይህ ሁሉ ኢህአዴግ ይዳን የሚል ድጋፍ ለመግለፅ ምን አገባህ የሚል ጥያቄ ከብዙ ሰው እጠብቃሎህ።ለዚህ የኔ መልስ እንደ አንድ ጤነኛ አገራዊ እይታ ያለው ዜጋ አገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ አገሬና ሰላሜ ዳግም ላላገኛቸው በቀማኞች ከተወሰዱብኝ በኋላ ትርጉም የሌለው ለቅሶ ከማልቀስ አሁን ባለው ሁኔታ የተደራጀና አገር ለማዳን በጣም የተሻለ እድል  ያለው ኢህአዴግን  ከመደገፍ የተሻለ አማራጭ እንደሌለ ከእርግጠኛም በላይ እርግጠኛ ስለሆንኩኝ ነው።ሌላው ደግሞ በጎንደር እንደ መላኩ ተፈራ ያለ ስርዓትና አሁን ደግሞ ህገ-ወጥ ሆኖ እያለም ሰው ላለመግደል ብሎ ራሱን ለመስዋእት የሚያቀርብ ስርዓት ልዩነትም አውቃሎህና ነው።

ሰላም ወርቅ ሁላገር

ሐምሌ 2008 ዓ/ም አ/አበባ

agerawiguday@gmail.com ወይም

በfacebook selamwerqhuluager እንገናኝ ።